# በሎንደን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በወያኔና በሱዳን መሀል የተደረገውን አገር ሻጬን የድንበር ውል አወገዙ።

ወንደሙ መኰንን፣ ሎንንደን ጥር ፱ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም



በሎንደን ከተማ፣ በኢትዮጵያ ተራድዖ ማኅበር አዳራሽ  ጥር ፱ ቀን ፪ሺ፪ ዓ ም የተደረገው ኅዝባዊ ስብሰባ፣ በወያኔ/ኢሕአዴግና በሱዳን መሀል፣ አሳሪነት በሌለው የቅኝ ገዢዎች መረጃ ላይ ተመርኵዞ የተደረሰውን ውል የአገርን ሉዓላዊነት የሚሺራርፍ በመሆኑ አወገዘው። ይኽ ዶክተር ኤርሚያስ ዓለሙ በሊቀመንበርነት የመሩት ሕዝባዊ ስብሰባ፣ ጥናታዊ ጽሑፎችና ከዚህ በፊት ተሰምተው የማይታውቁ መረጃዎች የቀረቡበት፣ ብዙ ትምሕርት የተቀሰመበት ስብሰባ እንደነበር ሁሉም በማድነቅ አዘጋጆቹን አመስግኗል።

ሊቀመንበሩ ስብሰባውን የከፈቱት፣ ለዲሞክራሲና ስብዓዊ መብት ሲታገሉ፣ የወደቁትን፣ ድንበሬን፣ ቄዬዬን፣ እርሻዬን፣ ቤቴን፣ ንብረቴንና አገሬን አላስደፍርም በማለት ሲፋለሙ የወደቁትን፣ በእስር ቤት የሚማቀቁትን በማስታውስ በጸሎት ከከፍቱት በኋላ፣ የጉዳዩን አሳሳቢነት በማየት የእሑድ ዕረፍታቸውን ሰውተው የመጡትን ተሰባሳቢዎች አመስግነው ሊቀ ማምራን አበባው ይግዛውን ስለድንበሩ ጉዳይ የመግቢያ ንግግር እንዲያደርጉ ጋበዙአቸው።



ቁም-ነገሩ፣ "ማን ይናገር የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ" እንደሚባለው ሆነና አካባቢውን በድንብ የሚያውቁት፣ ጎንደርን በምክትል አስተዳዳሪነት የመሩት ሊቀ ማምራን አበባው ይግዛው፣ ስለ አካባቢው ውበት፣ ልማት፣ በሚጣፍጥና በሚገባ አማርኛ ጥርት አድርገው አስረዱ። እጅግ አድርገው በሚያሳምን፣ ወኔ በሚቀሰቅሽ እና "ወይ አገሬ በሚያሰኝ" ሁኔታ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለምን እንዲህ ዓይነቱን የአገር ክህደት ወንጀልን መቋቋም እንዳለበት ሲያስረዱ፥ "ድንበሩ የተጣሰበት፣ ሰላም የለውም፣ ድንበር የሌለው ዜጋ እንቅልፍ የለውም፣ ድንበር የሌለው አገር ስለልማትና ዕድገት ሊያወራ አይችልም"ብለው ወገንን አስደምመወታል። ለምን በቆራጥነት መታገል እንዳስፈለገም በማያወላውል አኳኋን አስረድተዋል.። ከዚህ በፊት ተደፍሮ፣ ድንበሩ በባዕድ ሲገፋ፣ የመሪውን የክተት አዋጅ ሰምቶ በአንድነት "ሆ!"ብሎ ቀፎው እንደተነካበት ንብ ተነስቶ ክብሩን በክንዱ የሚያስጠብቅ ሕዝባችን፣ "መሪ ነኝ" ባዩ ከሀዲ ከሆነ ወዴት ይደረሳል? ዛሬ ከአንድ መንደር ተጠራርተው ወጥተው ለአገር መሪነት በተአምር በበቁት ከሀዲዎች ድንበሩ ሊደፈር፣ መሬቱ ሊቆረስ ያየ ሕዝባችን ግራ ተጋብቶአል። በነገራችን ላይ፣ ሊቀ ማምራን አበባው ይግዛው፣ በጣት ከሚቆጠሩት አዛውንት፣ አንድም ቀን ለአገራችን አንድነትና ሉዓላዊነት ከሚደረገው ትግል ጀርባቸውን እስካሁን ያልሰጡ፣  ከራሳቸው የጤንነት ሁኔታና ያልተመቻቸ የስደት ኑሮ ይበልጥ የአገራቸው ድኅንነት ዕንቅልፍ የሚነሳቸው "አይዞአችሁ! በርቱ!" ባይ አባት መካሪና ለነጻነት ታጋይ ናቸው። እኚሁ አባት ናቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የታሪክ ሊቆቻችን፣ በዚህ አክባቢ ብዙ ምርምር ሲያካሄዱ ያላዩትን ብዙ የተባለለትን ካርታ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ከተደበቀበት ጎልግለው አውጥተው ለማየት የበቁት። ያም ሳይበቃቸው፣ በልዩ ጥበብና ማግባባት ከብሪቲሽ ላይብራሪ ዝግ መዝገብ ቤት (archive) በረቀቀ ዘዴ ፎቶ ኮፒ ማድረግ ችለዋል። ካርታው፣ ከዚያም ተርፎ ዛሬ በአንዳንድ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ዕርዳታ በጨረር ፎቶ ተነስቶ (ስካን ተደርጎ) በኮምፕዩተር ለሚፈልገው ሁሉ ለመዳረስ ተችሏል። እንዴት አድረገው እንደተሳካላቸው አትጠይቁ። ብቻ፣ ፍላጎትና የአገር ፍቅር ያለው ምንም ማድረግ

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

እንደሚችል እኚህ አባት አስተማሩን። ሊቀ ማምራን አበባው ይግዛው፣ ኣጼ ምኒልክ ይኸችን ዛሬ በዕጃችን የቀረቺውን ኢትዮጵያን ለኛ ለማውረስ ብዙ ውጣ ወረደ አሳልፈዋል፤ ስንቱን አቀበት ወጥተው ስንቱን ቁልቁለት ወረደዋል ብለው ችግራቸውን ሁሉ አስረድተዋል። ከቅኝ ገዢዎች ጋር ባደረጉት ትንቅንቅ፣ በተለይ፣ ከለየላት ጠላት፣ ከጣሊያን ይልቅ፣ የእንግሊዝ ደባ ምንኛ እንዳስቸገራቸው፣ አስተምረውናል። በጊዜው አገሪቱ ውስጥ ተከስቶ የነበረው ረሀብ ምንኛ ሕዝባቸውን እንደጎዳባቸው፣ ገልጠዋል። ቢሆንም ለእንግሊዝ ማስፈራራትና ግፊት ሳይንበረከኩ የራስ ምታት እንድሆኑባት አስረድተው፣ ሊቀ ማምራን አበባው ይግዛው ለጥልቀቱ ጥናት፣ለቀድሞው የአዲስ አበባው ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ምሩቅ፣ ለአቶ አገኘሁ ገበየሁ መድረኩን አስረከቡ።



አቶ አገኘሁ ገበየሁ፣ ያቀረቡት ጥናትና የምርምር ውጤት ተመልካቹን ከአንድ ሰዓት ተኩል በላይ ከመቀመጫው ያጣብቀው፣ ተሰምቶ የማይሰለች፣ የዕውቀት ምንጭ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። የተሳካለት፣ በጥንቃቄ የተዘጋጀ፣ በማስረጃ የተደገፈ፣ ምሑርዊ ጥናት ነበር። ምሑራን እንኳን አንድን የምርምር ውጤት ሲያቀርቡ፣ ስልችት ይላሉ። አቶ አገኘሁ ግን፣ ረቂቁን ጥናት በሚገባ ቋንቋ፣ በአገር ፍቅር ስሜት ሸፍነውና አጣፍጥው አጎረሱን። ማንም ሰው ከተቀመጠበት ሳይነቃነቅ፣ የቅኝ ገዥዎች አፍሪካን ሲቀረማመቷት እንዴት አድረገው ኢትዮጵያን፣ ብቸኛዋን የአህጉሪቷን ነጻ ሀገር እንደከበቧት ቁልጭ አድረገው አስቀመጡ። ብሪቲሽ ላይብራሪ መዝገብ ቤት (archive) ውስጥ ተደብቀው አቧራ ሲጠጡ የነበሩትን፣ የእንግሊዞችን ሸርና ተንኰል አንድ በንድ የሚዘከዝኩ ሰነዶችን ቆፍረው አውጥተው አድማጩን “ይኽም ነበር ለካ!” አሰኝተውታል። የአባይን ምንጭ ለመቆጣጠር ግብጾች ለሺ ዓመታት ያደሩትን ድር፣ የወጉንን ጠርነቶች፣ በባሕል፣ በሀይማኖት ሳቢያ፣ ያደረሱብንን ጣጣ፣ የውስጥ ቅራኔን በመጠቀም እርስበርስ እንድንበላላ የሸረቡብን ሴራ አንዳች ሳትቀር ግልጥልጥ አድርገው አስተማሩን። የደርቦሾችን (መህዲስቶች) ቂም ያዘለ በቀል በመረጃ አስደግፈው አስረዱ። በኋላ ላይ፣ ሁለቱም አገሮች፣ ግብጽና ሱዳን እራሳቸው፣ የእንግሊዝ ቅኝ ግዝት ሆነው አረፋአት። ስማቸውን ተነጥቀው፣ ሕልውናቸውን አጥተው አንግሎ-እጂብሺያን ተሪቶሪስ ተባሉ። እንዲያም ሆኖ ግን፣ ኢትዮጵያ ነጻነቷን አስጠብቃ ኖረች። እንግሊዝ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ድንበር መካለል ነበረባት። ኢትዮጵያ ተከባ ነበር። ክምዕራብ እስከደቡብ፣ እንግሊዝ ሰፊውን ቦታ ይዛ ነበር። በደቡብ ምስራቅ እንግሊዝና ጣሊያን፣ ክምስራቅ፣ ፈረንሳይ፣ ከሰሜን ጣሊያን ከበዋት መፈናፈኛ አልነበራትም። በዚህ ጊዜ ነበር እንግሊዝ ትልቅ መሬት ቆርሳ ከኢትዮጵያ ለመንጠቅና አንግሎ-ኢጅፕሺያን ግዛቷ ውስጥ ለመጨመር ወጥመዱን የዘረጋቸው። መጀመሪያ ሀሪንግተን የተባለ እንግሊዛዊ ነበር፣ አጼ ምኒልክን አንዳንዴም በማግባባት ሌላ ጊዜም በማስፈራራት ከማይወጡበት ጣጣ ውስጥ ሊከታቸው ሊያጉላላቸው ይሞክር የነበረው። ብልሁ ንጉስ ዓፄ ምኒልክ ግን፣ ከወጥመዱ ብዙ ጊዜ አምልጠዋል። በጭንቀት (ዱረስ) ውስጥ እያሉ፣ ሥራ ላይ ያልዋለ ከምንም የማይቆጠር ውል በ1902 ንጉሱ ፈርመው ነበር። በኋላ ላይ አንድ ሻለቃ ጉዊን የሚባል እብድ እንግሊዛዊ፣ ስምምነቱንም ትቶ በራሱ፣ “ለአደንና ለሳይንሳዊ ጥናት” ፈቃድ ከንጉሱ አስወጥቶ እየዞረ፣ ደስ ያለውን መሬት ወደ እንግሊዝ ግዛት እየሞጀረ በርሱ ምኞች ካርታ ይስል ገባ። አቶ አገኘሁም ስለዚህ የጠር መኰንን ሲናገሩ የስለላ ካርታ ሲስል ምን ያደርግ እንደነበረ፣ ጠላትን የጎሪጥ ያይ የነበረው የአገሬው ሕዝብ ሲጠይቀው እንዳይተናኮለው ለአደንና ለሳይንሳዊ ጥናቱ ጉዞ ላይ እንደነበረ የሚያስረዳ የንጉሡን ደበዳቤ እያወጣ ያሳይ ነበር ብለዋል።

“Major Gwynn & Major Austin instructed by the British government ‘to pose as semi-scientific, semi-shooting expedition, and to avoid discussing frontier questions with anyone except possibly Abyssinian officers of some rank whom we might meet.’”

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ በማጭበርበር አንድ ሻለቃ የነደፈውን ካርታ ነበር፣ አቶ መለስ ሆዬ ከመቃብር ቆፍረው አውጥተው ለወዳጃቸው፣ ለሱዳን መንግስት የኢትዮጵያን አንጡራ መሬት ሊያስረክቡ የደፈሩት።

ጥናቱ ሰፊ ስለሆነ፣ ዋናው የአቶ አገኘሁ ሥራ በድረገጾች የውስጥ መረብ (internet) እንዲበተን ሕዝቡ ስለጠየቀ በቅርቡ የኸው የፈጸማል።



ከዚህ በኋላ ወለሉ ለውይይት ተከፍቶ ሰፋ ያሉ አስተያየቶችን አስተናግዷል። በውይይቱ ጊዜ፣ የሕግ ጉዳይ በሕግ ባለሙያዎች ተነስቶ በቂ ምላሽ ተሰጥቶታል። ይኸን የሞተ ውል፣ ወያኔን ምን ከመቃበር አስነሳታት? መሬታችንንስ ለጎረቤት አገር እንዲህ ለመቸር ምን አነሳሳት የሚል ጥያቄም ተነስቷል። መድረኩ የመሰለውን መልስ ቢሰጥም፣ እንዲህ ዓይነት ወንጀል በአንድ መንግሥት ሲፈጽም በታሪክ የኸ የመጀመሪያው በመሆኑ ዕውነተኛውን ሀቅ ሊያውቅ የሚችለው እራሱ የወንጀሉ ፈጻሚ ወያኔ ብቻ ነው።

ሌላው ታዳሚ የጠየቁት ጥያቄ ወያኔ እንዲሕ ዓይነት ክሕደት በዚህ ሰዓት ሲፈጽም፣ ምናልባት



በምርጫው እንዳንረብሸው የቤት ሥራ ሰጥቶን እዚያ ላይ ብቻ እንድናተኩር ታስቦ ይሆን የሚል ነበር። ከአዳማጩ መሐልና ከመድረኩም በጣም ጠልቅ ያለ መልስ ተሰጥቶበታል። ወያኔ የኸ ጎዱ እንዳይታወቅበት አፍኖ ለመደበቅ ሞክሯል፣ ፈርቶ፣ ተምቦቅቡቋል። በምስጢር የያዘውም በዚህ ምክንያት ነበር። የሱዳን መንግሥት ግልጽ ሲያደረገውም በጣም ተናደባቸው ነበር። ስለዚህ ይኸ ወያኔ እንዲነሳበት የማይፈልገው፣ ጨለማን ተገን አድረጎ ኢትዮጵያን ሊጎዳት የሸረባት ደባ ነበርች። ሊያመልጥ የሞከረበት አሳፋሪ ድርጊት በመሆኑ፣ ብዙዎቻችን ያንን ጉዳይ ይዘን እንደንነሳ ጨርሶ አይፈልግም። ያውቃታላ!!! ኢትዮጵያዊ ለድንበሩና ለትዳሩ ቀናዒ የሆነ ሕበረተሰብ ነው። ወያኔ ያንን ጠንቅቆ ያውቃል። ስለዚህ እኛ ስለምርጫው ጉዳይ ሳይሆን የአገር ማትረፉ ትግል ላይ ማትኮር እንዳለብን በደንብ ተቀምጧል። ከብዙ የሀሳብ ልውውጥም በኋላ፡ ሕዝቡ የሚከተለውን የአቋም መግልጫ አውጥቷል።





“በዛሬው ዕለት ጥር ፱ ቀን ፪ሺ፪ ዓ. ም. በሎንደን ከተማ በኢትዮጵያውያን ተራድዖ ማኅበር አዳራሽ የተደረገው የኢትዮጵያውያን ሕዝባዊ ስብሰባ በኢትዮጵያና በሱዳን መሀከል ስላለው አሳሳቢ የድንበር ማካለል ጉዳይ ጠለቅ ያለ ምርምር የተካሄደበት ጥናት ቀርቧል። አሳማኝ መረጃዎች ለተሰብሳቢው ሕብረተሰብ ቀርቦ፣ ጥልቀት ያለው ግንዛቤ ለማስጨበጥ ተችሏል። ተሰብሳቢው ጥናቱን በጥሞና ካዳመጠ በኋላ በሰፊው ተወያይቶበታል። የድንበሩ ጉዳይ በጣም አሳሳቢና አደገኛ ሁኔታ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ተገንዝቧል።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ከዚህ ጭብጥ በመነሳት፣ ሎንደን ኗሪ የሆንን ኢትዮጵያዊያን በዛሬው ዕለት የሚከተሉትን የአቋም መግለጫ ተስማምተን አስተላልፈናል።

ሀ) ባለ ጉዳዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይወያይበት፣ ከጀርባው በምስጢር፣ ወያኔ/ኢሕዴግና የሱዳን መንግሥት የተስማሙበትን የድንበር ውል፣ አገራዊ ክህደት ሲሆን፣ ልክ ከዚህ በፊት እንደተደረገው የአገሪቷን ሉአላዊነት የሚሸራርፍና የኢትዮጵያን አንጡራ መሬት ለሱዳን አሳልፎ የሚሰጥ ደባ መሆኑን በመገንዘብ፣ ድርጊቱን እናወግዘዋለን።

ለ) የኢትዮጵያው አምባገነን ገዢ፣ በሕዛባችን ጀርባ፣ በምስጢር ከሱዳን መንግሥት ጋር ሲደራደር፣ ከሱዳን መንግሥት በኩል ብቻ አንዳንድ የራሳቸውን የደስታ መግለጫዎች ሲያወጡ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በወያኔ መንግስት በኩል ምንም መረጃ እንዳያገኝ የተደረገበትን ደባ ሙሉ በሙሉ እንቃወመዋለን።

ሐ) የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በድንበራችን አካባቢ ያለውን ሰፊ መሬት ለሱዳን በድብቅ አሳልፎ ሲሰጥ፣ ለስሙ የሕዝብ ተወካዮች ናቸው በሚባሉት በምክር ቤቱ/ፓርላማ የገጠገጣቸው ሰዎች እንኳን ሳያውቁ ክሕደት ፈጽሟልና፣ በራሱ ሕገ መንግሥት ሳይቀር ውክልና እንንደሌለው አረጋግጧል።

መ) ወያኔ/ኢሕአዴግ የሕዝብ ውክልና ሳይኖረው ባለጉዳዩን ሕዝብ ሳያማክር በጉልበት አስገደደ፣ ኗሪውን ከቀዬው ፈንቅሎ፣ ከሱዳን መንግሥት ጋር የፈጸመውን ውል፣ ከዚህ በፊት በዋናው ኮሚቴ እንደተላለፈው ሁሉ፣ ወደፊትም እንደ ሕጋዊ ድርድር ቆጥረን ልናከበረው እንደማንችል፣ ለአፍሪክ ሕብረት፣ ለሱዳን መንግሥትና ለዓለም ሕብረተሰብ ከውዲሁ ልናስታውቅ እንወዳለን።

ሰ) ለሱዳን በድብቅ የተሰጠው መሬት፣ አባቶቻችን ደማቸውን አፍስሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው በታሪክ ያቆዩልን የሉዓላዊነታችን ማረጋገጫ ነውና አገር ሻጩ የወያኔ መንግሥትና ግብረ አበሮቹ እንዲሕ ዓየነቱን አሳሪነት በሌለው ውል አመካኝተው የአገር ክህደት ወንጀል ሲፈጽሙ፣ የተዋዋሉት ውል ምንም ዓየነት ሕጋዊ ውክልን እንደሌለው ሊታወቅ ይገባል።

ረ) የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪካዊ ድንበሩንና መሬቱን፣ እያንዳንዷን የእርሻ ማሳ ሳታቀር ጠንቅቆ ያውቃታል። በመሆኑም፣ ሜዳውን፣ ጋራውን፣ ቆላውንና ደጋውን፣ ወንዙንና ማንኛውንም የአገሩን ሉዓላዊ ድንበሩን ሲከላከል ኑሯል። ስለዚህ፣ በሕዝባችን ጀርባ በወያኔና ጭፍሮቹ መሀል በማናለብኝነት የተፈጸመው ውል ቢኖር፣ የአገርን መሬት ቆርሶ ለባዕድ መስጠቱን፣ ምንጊዜም የምንቃወመውና የማናከበረው መሆኑን ከወዲሁ ልናስረግጥ እንወዳለን።

ሠ) ቤታቸውን፣ ንብረታቸውን፣ እርሻቸውን፣ ድንበራቸውን ላለማስደፈር ሲፋለሙ ከተጎዱት የአካባቢው ኗሪ ወገኖቻችን ጎን አብረን መቆማችንን እናስታውቃለን። በአሁኑ ሰዓት መብታቸውን ለማስከበር የሚጠቀሙበትን ማንኛውንም እርምጃ እንደግፋለን።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ሸ) ይኸ የወያኔ/ኢሕአዴግ የአገር ክህደት ወንጀል ድርጊታቸው ተመዝግቦ፣ ባለሥልጥናቱ የፈጸሙት ወንጀል ወደፊት እንደሚያስጠይቃቸው ከወዲሁ እናሳስባለን። ከወያኔ ጋር አብረው እንዲህ ዓይነቱ የሀገር ክህደት ወንጀል ሲፈጸም የተባበሩአቸው ደጋፊዎቻቸውም በሕግና በታሪክ ፊት ወደፊት እንደሚጠየቁበት ልናሳስብ እንወዳለን።

ቀ) ለተቃዋሚ ፓርቲዎችና  የሲቪክ (የሙያና የሰበአዊ መብት ተከራካሪ) ማኅበራት እንዲሁም የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት የሚያሳስባችሁ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፣ ወያኔ/ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመውን ደባ በአንደነት እንድናወግዝ፣ አደጋውንም ለመከላከል አብረን እንድንታገል፣ ጥሪአችንን እናስተላለፋለን።

በ) በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሚገኙ ነጻ የመገናኛ ብዙሀን ሠራተኞች፣ ይኸንን ዓብይና አሳሳቢ ጉዳይ በማስመለከት በወያኔ ኢሕአዴግ በኩል ሲፈጸም የቆየውን ቅጥፈት በተጨበጠ ማስራጃ በማጋለጣቸው ተሰብሳቢው ሊያመሰግናቸው ይወዳል። ወደፊትም እንዲቀጥሉ እንጠይቃለን።”

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!
ትግሉ ይቀጥላል!

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com